# ስለ ታዳጊ ጆች እና ስለ ማሪዋና ዕውነታዎች

## የተወሰኑ መልካም (እና አስገራሚ) ዜናዎች እዚህ ቀርበዋል፦
## በማሪዋና እና በሌሎች ዕፆች አጠቃቀም ዙሪያ፣ ታዳጊ ልጆች ወላጆቻቸውን እና ሌሎች የሚታመኑ አዋቂ ሰዎችን ተሞክሮ ለህይወታቸው በተሞክሮነት ይወስዳሉ።

ከዚህም በላይ መልካም የሆነም ዜና ይኸውልዎት፦ **ከልጆች ጋር መነጋገር በትክክል እንደሚሰራ እናውቃለን።** በመኪና ውስጥ፣ በእራት ላይ ወይም በሰፈር ጉዞ ላይ እያሉ ሊሆን ይችላል፣ ስለ ማሪዋና መጠቀም ከታዳጊ ልጅዎ ጋር ሲያወሩ፣ እያዳመጡዎት ነው።

ጥያቄዎች ይኖራቸዋል፣ እናም መልስ መስጠት እንዳለብዎት ከተሞክሮ ያውቃሉ።

### እናም... ማሪዋና በታዳጊ ልጆች ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ያሳድራል?

1. ማሪዋና በትምህርታቸው ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። ቀደም ብሎ ማሪዋና መውሰድ የልጆች አዕምሮ ዕድገት ላይ ለውጥ ያመጣል እንዲሁም በማስታወስ ችሎታ፣ በትምህርት እና በእውቀት ላይ ዘላቂ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድራል።

2. ማሪዋና ከአዋቂዎች በበለጠ በታዳጊ ልጆች ላይ ሱስ የማስያዝ አቅም አለው፡፡ ዋሽንግተን ውስጥ፣ ወደ የዕፅ ህክምና ፕሮግራም የሚገቡ አብዛኞቹ ታዳጊዎች በዋናነት የሚጠቀሙት ማሪዋና እንደሆነ ሪፖርት አድርገዋል።



3. ማሪዋና መጠቀም ሰውነትን የማስተባበር እና ምላሽ የመስጠት ፍጥነትን የሚቀንስ ሲሆን ዋሽንግተን ውስጥ፣ በተለይ ከሌሎች ዕፆች ጋር ሲቀላቀል ሞት ከሚያስከትሉ የመኪና ግጭቶች ጋር ይያያዛል።

4. ማሪዋና መጠቀም የማይጠበቅ ባህሪ እና ደካማ የውሳኔ አሰጣጥ እንዲኖር በማድረግ ተጠቃሚው እና ሌሎችም ለአደጋ እንዲጋለጡ ያደርጋል።

5. ከ 21 ዓመት በታች ያሉ ሰዎች ማሪዋና መጠቀም ህግ መጣስም ነው። ይህ ህግ ብዙ ጊዜ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተፈጻሚ ስለማይሆን ማሪዋና መጠቀምን ማስወገድ ታዳጊ ልጆች ከህግ አስከባሪዎች እና ከሌሎች የወንጀል ህግ ስርዓት ጋር መስተጋብር እንዳይኖራቸው ያስችላል። ከዕፅ ጋር በተገናኘ በቁጥጥር ሰር መዋል እና ተያይዞ የሚመጣው ትችት ወደፊት ሥራ እና ለኮሌጅ የፋይናንስ ድጋፍ የማግኘቱን ጥረት ከባድ ያደርገዋል።

አሁን እውነታዎችን አውቀዋል፣ **ማሪዋና መጠቀም ሊኖረው ስለሚችለው አደጋ ከታዳጊ ልጅዎ ጋር ይነጋገሩ**። ስለሚያወጧቸው ህጎች እና የሚጠበቁ ጉዳዮች ግልፅ ይሁኑ። በማንኛውም ሰዓት ሊረዷቸው ዝግጁ መሆንዎን ይናገሩ።

ለተጨማሪ መረጃ እና ስለ ዕውነታዎች የበለጠ ለመረዳት፣ **StartTalkingNow.org** ን ይጎብኙ። ልጅዎ ጤናማ ምርጫዎችን ስለመምረጥ የበለጠ ማወቅ ከፈለገ/ከፈለገች፣ **YouCanWA.org** ላይ መመልከት ይችላል/ትችላለች።

ታዳጊ ልጅዎ ከአቻው/ዋ ጋር ለማውራት የበለጠ ምቾት ከተሰማው/ከተሰማት፣ ስልጠና የወሰዱ ታዳጊዎች የሚሰሩበት ሚስጥራዊ እና ነፃ የእገዛ የጥሪ መስመር አለ። ልጅዎ **1-866-TEENLINK (833-6546)** ላይ በመደወል፣ በፅሁፍ ወይም በፅሁፍ ምልልስ እንዲያነጋግሩ ያበረታቷቸው።

ልጅዎ በማሪዋና ወይም በሌሎች ዕፆች መጠቀም ምክንያት እየታገለ/ች እንደሆነ ካሰቡ፣ ሀኪም ያነጋግሩ ወይም ለ **Washington Recovery Help Line ከ 1-866-789-1511** ላይ ይደውሉ።

Washington State Department of Health